# ወራሪው የሱዳን ጦር ድባቅ ተመቶ ተባረረ ፤ 8 የሱዳን ወራሪዎች ተማረኩ

**ከኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ የተሰጠ መግለጫ**

ግንቦት 2 ቀን 2000 ዓ.ም. ( May 10, 2008 )

ከጥቂት ቀናት በፊት የሱዳን ጦር የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ጥሶ በመግባት በጎንደር ክፍለ ሃገር በቋራ ወረዳ ያካሄደውን ወራራ ፣ ዝርፊያና ንብረት ማውደም ለመድገም ፤ በከባድ መሣሪያ የተደራጀው ይኸው ወራሪ የሱዳን ጦር ሐሙስ ሚያዝያ 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ( May 8, 2008 ) በዛው በጎንደር ክፍለ ሃገር ፣ ታች አርማጭሆ ወረዳ ዘልቆ በመግባት ከአብደራፊ ከተማ ወጣ ብሎ በስተምዕራብ በኩል ከገላአሉባን እና ጓንግ ወንዝ መካከል የሚገኘውን የአቶ አራዶም ተወልደ መድህን የእርሻ ልማት በመዝረፍና በማቃጠል ላይ እንዳለ ፤ የሃገሩን ዳር ድንበር በቆራጥነት ለማስከበር በከፍተኛ ወኔ ታጥቆ የተነሳው የአካባቢው ሕዝብ የክተት ጥሪ በማሰማት ከወራሪው የሱዳን ጦር ጋር ከፍተኛ ፍልሚያ አካሂዶ ድል ከተቀዳጀ በኋላ ፤ ወራሪውን ጦር እየተከታተለ ድባቅ በመምታት ወደ መጣበት አባሮ ከመመለሱም በላይ ፤ በውጊያ ላይ የነበሩ 8 የሱዳን ወራሪዎችን ማርኮ በቁጥጥር ሥር አውሏል።

እንደሌሎቹ ኢትዮጵያውያን ወገኖቹ ለሃገሩ ነፃነት ቀናዒነት ያለውና የሃገሩን ዳር ድንበር በማስጠበቅ ከፍተኛ ተጋድሎ የሚያደርገው ይኸው የአካባቢው ሕዝብ ዳር ድንበሩን ከወራሪው የሱዳን ጦር ለማስከበር በሚያካሂደው መራራ ትግል የወያኔ/ኢሕአዴግ መንግሥት ጣልቃ እንዳይገባበት ለአካባቢው ባለሥልጣናት አስታውቋል።

የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት በቆራጥ ልጆቿ ይከበራል!

የሀገራችንን ዳር ድንበር ለማስከበር የአባቶቻችን ቃል-ኪዳንና አደራ አለብን!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

የኢትዮጵያና ሱዳን ድንበር ጉዳይ ኮሚቴ
ኢሜል አድራሻ/ E-mail: leethiopia@yahoo.com

EthioLion.com